# የKING COUNTY የጎርፍ አደጋ ማገገሚያ



## 1 የመደን አቅራቢዎን ያነጋግሩ




ለቤት፣ ለመኪና፣ ለተከራዮች ወይም ለንግድ መደን የይገባኛል ጥያቄ ከመደን አቅራቢዎ ጋር ማቅረብ በአደጋ ጊዜ ለማገገም የመጀመሪያው እርምጃዎ ነው። የንብረትዎን ውድመት የሚያሳዩ የመመሪያ ሰነዶችን እና ፎቶዎችን ለማቅረብ ዝግጁ መሆን አለብዎት።

## 2 ወደ 211 ይደውሉ

የመኖሪያ ቤት፣ የምግብ ወይም የአእምሮ ጤና ምክር ከፈለጉ ወደ 211 ይደውሉ። ሁሉም ግብዓቶች ነጻ ናቸው እና ጥሪዎች ሚስጥራዊ ናቸው። እንዲሁም www.211.org የሚገኙ አገልግሎቶችን ማሰስ ይችላሉ

## 3 ማጽዳት እና መልሶ መገንባት



አደጋ በኋላ መልሶ መገንባት ረጅም እና ውስብስብ ሂደት ሊሆን ይችላል። የጥገና፣ የተተኪ ዕቃዎች ግዥ እና የማናቸውንም ከአደጋው ጋር ለተያያዙ ወጪዎች ደረሰኞች በጥንቃቄ ይያዙ። እነዚህ ወጪዎች በኢንሹራንስ ሰጪዎ ወይም በመንግስት የእርዳታ ፕሮግራሞች አማካኝነት ተመላሽ ሊደረጉልዎ ይችላሉ። ማጭበርበሮችን ያስወግዱ! ኮንትራክተሮች በዋሽንግተን ግዛት የሰራተኛ እና ኢንዱስትሪ መመሪያ (L&I) በኩል የሙያ ፈቃድ ያላቸው መሆኑን ያረጋግጡ።

## 4 የጉዳት ዳሰሳ ጥናቱን ይሙሉ

የKing County የአደጋ ጊዜ አስተዳደር በቅርቡ የተከሰተውን የጎርፍ አደጋ ተከትሎ የሚመጣውን ጉዳት በመገምገም ላይ ነው። እባክዎ በግል ንብረትዎ ወይም በንግድ ድርጅትዎ ላይ ተጽዕኖ ካጋጠመዎ፣ የተጽዕኖ ዳሰሳ ጥናቱን ያስገቡ።

ለመኖሪያ ቤት ተጽእኖዎች (ተከራዮችን ጨምሮ) ወደሚከተለው ይሂዱ፦ የKCOEM ነዋሪዎች ላይ የደረሰ ተጽዕኖ ዳሰሳ ጥናት

ንግድ ላይ ለደረሱ ተጽዕኖዎች ወደሚከተለው ይሂዱ፦ የKCOEM ንግድ ላይ የደረሱ ተጽዕኖ ዳሰሳ ጥናት.

## ለተጨማሪ ቋንቋዎች ይቃኙ

አረብኛ
ስፓኒሽ
ቻይንኛ
ቪየትናምኛ
ታንጋሎግኛ
ሶማሊኛ
ሩሲያኛ
ኮሪያኛ
ዩክሬንኛ
አማርኛ

KINGCOUNTY.GOV/FLOODRECOVERY

King County

ዲሴ 2025/ ጃን 2026

King County

# የጎርፍ አደጋ ማገገሚያ ግብዓቶች

| | | |
|---|---|---|
| **Washington Department of Social and Health Services (DSHS)** | ብቁ ለሆኑ ቤተሰቦች የሚሰጥ የአደጋ ጊዜ የገንዘብ እርዳታ | **877-501-2233**<br>DSHS.WA.gov |
| **King County Department of Community and Human Services (DCHS)** | በአብዛኛዎቹ የKing County አካባቢዎች ውስጥ ለሚገኙ ዝቅተኛ እና መካከለኛ ገቢ ላላቸው የቤት ባለቤቶች እንዲሁም አካል ጉዳተኛ ለሆኑ ተከራዮች የቤት እድሳት እርዳታ ያቀርባል። | **206-263-9095**<br>KingCounty.gov/DCHS |
| **Crisis Cleanup** | ቤተሰቦችን ከነፃ የጎርፍ ጽዳት አገልግሎቶች ጋር ያገናኛል | **844-965-1386** |
| **Public Health Seattle & King County (PHSKC)** | የጎርፍ ጽዳት ጥንቃቄዎች እና የሻጋታ መከላከያ መንገዶች ላይ ያለ መረጃ | **206-296-0100**<br>KingCounty.gov/Health |
| **King County Department of Local Services** | የከተማ አስተዳደር ውስጥ ላልተካተቱ የKing County ነዋሪዎች የሚሰጥ የጎርፍ አደጋ መገገሚያ ፈቃድ በከተማ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚኖሩ ነዋሪዎች የየከተማቸውን ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ማነጋገር አለባቸው። | **206-296-6600**<br>KingCounty.gov/Local-Services |
| **King County Solid Waste Division** | እስከ ጃኑዋሪ 3፣ 2018 ባሉት ቅዳሜ እና እሁዶች በቦው ሌክ፣ በሾርላይን እና በኤንምክላው የቆሻሻ ማስተላለፊያ ጣቢያዎች የጎርፍ ፍርስራሾችን በነፃ ማስወገድ ይቻላል። | **206-477-4466**<br>KingCounty.gov/Solid-Waste |
| **Washington State Office of the Insurance Commissioner** | ስለ የቤት መድን እና የአደጋ ማገገምያ የሚገልጽ መረጃ፣ በመድን ድርጅቶች ላይ ቅሬታዎችን ያቅርቡ | **360-725-7000**<br>Insurance.WA.gov |
| **Washington Department of Labor & Industries** | ሥራ ተቋራጭ ወይም ሌላ ንግድን ያረጋግጡ | **360-902-5800**<br>LNI.WA.gov |
| **Disaster Distress Helpline** | ለአደጋ ሰለባዎች ነፃ የስልክ ወይም የጽሑፍ መልእክት የምክር አገልግሎት | **800-985-5990**<br>Call or SMS Text |

## 5 ማንቂያዎችን እና ዝማኔዎችን ያግኙ

Alert King County ለKing County የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ እና መረጃ የሚሰጥ መድረክ ነው። እንዲሁም ከተማዎ የራሱ የሆነ የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያ መድረክ ሊኖረው ይችላል። ከታች ያለውን የQR ኮድ በመጠቀም በመመዝገብ፣ የጎርፍ ማገገሚያ መረጃዎችን እና የአደጋ ጊዜ ማስጠንቀቂያዎችን በስልክዎ ወይም በኢሜልዎ እንዲደርስዎት ያድርጉ።

QR ኮዱን ይቃኙ ወይም ወደ kingcounty.gov/alert ይሂዱ

ALERT KING COUNTY